PANORAMA # XXXIV

# የትዝብት አድማስ

ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓም

## እጀ አመድ- አፋሽ የሆነች ሀገር

ዘወትር ቢለግስ፥ ቢቸር፥ ቢያበላ-ቢያጠጣ፥ "እጁን ቆርጦ ቢሰጥ" ቢታደግ-ቢጋፈጥ፥ ዋስ ቢቆም-ቢያስፈታ፥ እናም ደግሞ፥ ከሚጠበቅበት በላይ፥ መሥዋዕት ቢከፍል፥ በአጋጣሚም ይሁን በሌላ ምክንያት፥ የማይመሰገንና ተግባሩ የማይታውቅለት ሰው/ሀገር በየትኛውም ኅብረተሰብና ዓለም ውስጥ እንዳለ የታወቀ ነው:: አንዳንዱ የሚፈፅመው መልካም ተግባር፥ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ማድረግ/ መፈፀም ያለበት ነው ከሚለው መተከላዊ ዕምነት በመነሳት ስለሆነ ፥ተመሰገነ አልተመሰገነ፥ተግባሩ ታወቀለት አልታወቀለት ደንታ ላይሰጠው ይችላል:: ትክክለኛውም የሰው ልጅ ባኅርይና ተግባርም ይህ ነው ብለን እናምናለን:: በአንፃሩ ደግሞ፥ውለታ ለማግኘትና ለውዳሴ-ከንቱ ተብሎ የሚፈፀመው አድራጎት ግን፥ ከምግባረ ሰናይ ጋር ሊደመር የሚችል አይሆንም:: በዚህም ተባለ በዚያ፥ የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው ግን፥ የመልካም አድራጊው ተግባር አለመታወቁ ብቻ ሳይሆን፥ ድርጊቱን መካድና እንዲያውም በጎ አድራጊውን ለማጥፋት መሞከሩ ነው:: ይህንን ሲታዘብ፥ መልካም አድራጊው " እጄ አመድ አፋሽ ሆነብኝ" ለማለት ይገደዳል::

የዛሬይቱ ኢትዮጵያም፥ ያኀረሰችባቸው እጆቿ፥ እየተነከሱባት ስለሆኑ፤ የታሪክ ታዛቢዎቿ ሁሉ፥ " እጀ-አመድ አፋሿ ኢትዮጵያ" እያሉ ያዝኑላታል:: ጠላቶቿ ደግሞ፥ "ቂሏ ኢትዮጵያ " እያሉ ነው የሚያፌዙባት:: ይህንን ማውሳታችን ያለምክንያት አይደለም:: ይህንን ርዕስ ዛሬ ልናነሳው የተገደድንበት የራሱ የሆነ መንስዔ ስለአለው ነው:: ኢትዮጵያ ሀገራችን ለመላው ዓለም በጠቅላላው፥ ለአፍሪካ አህጉር ደግሞ በተለይ፥ ያበረከተችውን አኩሪና መሠረታዊ አተዋፅዖም ሆነ የከፈለችውን መሥዋዕት ስናስታውስ፥ በአንፃሩ ደግሞ ዛሬ የሚፈፀምባትን ደባና ተንኮል ስንከታተል፥ ወደፊት ልንከተለው የሚገባን የውጭ ፖሊሲ፥ ዲፕሎማሲና የዓለምአቀፍ ግንኙነት ምን መሆን እንደሚገባውና፥ ብሎም፥ ወዳጅ ጠላታችንን ለይተን ልናውቅ የሚያስችለንን ዘዴ ለመቀየስ የሚያስችለንን የዉጭ ፖሊሲ መንደፍ እንደሚገባን ለማሳሰብ ነው:: ይህ ተግባር በአሁኑ ወቅት ምናልባት እንደ አጣዳፊ አጀንዳ ሊታይ አይችል ይሆናል:: በዕርግጥም ዛሬ ከሁሉ አስቀድሞ ወያኔን አስወግዶ ሀገርን ማዳን መሆኑን የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛ አጀንዳ እንደሆነ እኛም እናምንበታለን:: በመሠረቱ፥ ሀገርና ሕዝብ ሲኖሩ ብቻ ነው፥ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንዲሁም የውጭ ፖሊሲዎች ሊነደፉና ሊወጡ የሚችሉት:: ሀገር ከሌለ ሌላው ሁሉ ከንቱ ይሆናል:: ያም ሆኖ ግን በአንድ ዐብይ ጉዳይ ላይ አስምረን ማለፍን እንሻለን:: ይኸውም፥ በትግላችን ሂደትና በዚህ የሀገራችን ቀውጤ ዘመን፥ የሕዝባችን ቀንደኛ ጠላቶች እነማን እንደሆኑ መረዳት፥ ለወደፊቱ የውጭ ፖሊሲያችን ራዕይና ንድፍ ሊረዳን የሚችል መሠረተዊ ግንዛቤ ማግኘት ጠቃሚ መሆኑን ነው::

ይህንን ለመገንዘብ ደግሞ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ቢያንስ ላለፉት ግማሽ ምዕተ -ዓመት የተከተለችውን የዉጭ ፖሊሲና ያከናወነችውን ተግባር በጥሞና ለመመርመር እንገደዳለን፡፡ በዲፕሎማሲው አውድማ፥ “ ዘላቂ ወዳጅም ይሁን ጠላት የሚባል ነገር አይኖርም፥ ሊኖር የሚችለው ዘላቂ ጥቅም ብቻ ነው” የሚባለውን መሠረታዊ ብሂል ሳንዘነጋ፥ ዛሬ በወያኔ የዘር ፖሊቲካ የምትማቅቀው ሀገራችን፥ የጎረቤት ወዳጅም ይሁን የእሩቅ ዘመድ እንደሌላት መረዳት ይኖርብናል፡፡ ይህንን ሀቅ ካልተገነዘብን፥ ለአለፉት ስድሳ ዓመታት በመርህ ላይ የተመሰረተም ይሁን በየዋኀነት ስንከተለው--ስንፈፅመው የኖርነውን፥ ነገር ግን ዛሬ በችግራችን ወቅት ሊረዳን ያልቻለውን ተላላነት ለመድገም እንችል ይሆናል ብለን እንሰጋለን፡፡ ይህ ስጋት ግን ዛሬ ወያኔ የሚከተለውን የሀገር ክኀደት መመሪያን አይጨምርም፡፡ ምክንያቱም፥ የወያኔ መሪዎች እንኳን በዕቅድ ወይም አስበውበት፥ ተሳስተውም ቢሆን ለኢትየጵያ መልካም ያስባሉ የሚል ብዥታ ሊኖር ስለማይችል ነው፡፡

እረ ለመሆኑ ለአለፉት አምሳና ስድሳ ዓመታት የሀገራችን የውጭ ፖሊሲ ምን ይመስል ነበር? ኢትዮጵያስ የዓለም ዓቀፍ ግንኙነቷና የዲፕሎማሲ አሰራሯ እንዴት ነበር? በዚህ ረድፍስ ለዓለም ምን ያደረገችው አስተዋፅዖ ነበራት? ለአፍሪካ ሕዝቦችና ለሦስተኛው ዓለም ምን ፈፀመች? ወዘተ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በሰፊው መመርመሩን፥ የኢትዮጵያን የዲፕሎማቲክ ታሪክ ለሚከታተሉ ተመራማሪዎች እንተወውና፥ ለተነሳነበት ዓላማ ማጠየቂያ ይሆኑን ዘንድ በአንድ አንድ ዓበይት በሆኑ ዕውነታዎች ላይ ማተኮሩን መርጠናል፡፡

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት መሥራች አባልነቷ ግዴታዋን ለመወጣት ስትል በአምሳዎቹ ዓመተ-ምህረት፥ሠራዊቷን ወደ ሩቅ ምሥራቅ ወደ ኮሪያ አዝምታ የዓለምን የጋራ ፀጥታና ሰላም አጠባበቅ( Collective Security) በሚል ሽፋን ለአሜሪካ ብሄራዊ ጥቅም ተዋድቃለች፡፡ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1956 ዓም የእንግሊዝ፥ የፈረንሳይና የእሥራዔል መንግሥታት በመተባበር በግብፅ ላይ ወረራን በአካሄዱባት ወቅት፥ ከመተከላዊ አቋሟ (Principle) አኳያ ወረራውን በመቃወም፥ የፀጥታው ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ በሎንዶን እንዲጠራ አስደርጋ ወረራው ተወግዞ ወራሪዎቹም ከስዊዝ ካናል የጦርነት ቀጠና በፍጥነት እንዲወጡ የሚለውን ውሳኔ እንዲተላለፍ ምክንያት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ነበረች፡፡ እንግዲህ ተመልከቱ፥ ዛሬ ግብፅ በሀገራችን ላይ የምትፈፅመውን ደባ! ተገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች የግብፅን ሁለንተናዊ ድጋፍ አግኝተው ዓላማቸውን ለማሳካት በቅተዋል፡፡ ግብፅ፥ የዓባይን ወንዝ፥ በዘለዓለማዊ መልኩ ለመቆጣጠር የነበራትን ኀልም ዕውን ለማድረግ ከመቸውም ጊዜ አመች ዕድል ያገኘችው ዛሬ ሆኖላታል፡፡ በትውልድና በዜግነት ኢትዮጵያዊ ሆኖ በተግባር፥ በባኀርይና በሰብዕና ግን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አበክሮ የሚያጠፋ ዘረኛ ቡድን በኢትዮጵያ ሥልጣን እንዲይዝ አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ በታሪኳ ዛሬ ተዳክማ ተከፋፍላ፥ ለብሔራዊ ጥቅሟ የቆመ መንግሥት አጥታ በአለችበት ወቅት፥ ግብፆች “ላሜ ወለደችልን” ብለዋል፡፡ አባይን ለመቆጣጠር እንዲያስችላቸውም ከወያኔ መሪዎች ጋር አስፈላጊውን ትብብርና ስምምነት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ሁሉም ሀገር ዘላቂ ጥቅሙን ለማስጠበቅ ማነኛውንም ሁሉ እንደሚያድርግ ስለ

እምንረዳ ግብፆች፥ ከወያኔ ጋር ቢተባበሩ አያስደንቀንም። ኢትዮጵያም፥ "ወርቅ ላበደረ ጠጠር" እያለች ሙሾዋን ትደረድራለች። ወደፊት ግብፅ የሕዝቧ ቁጥር እየጨመረና የውሃው መጠን እያጠረ በሚሄድበት ወቅት፥ የአባይን ምንጭ በስፋት ለመቆጣጠር እንዲመቻቸው፥ ግብፆች ኢትዮጵያ ተንኮታኩታ እንድትወድም የወያኔን ያላሰለሰ ትብብር እንደሚያስፈልጋቸው በሚገባ ተረድተውታል።

በ60ዎቹ ዓ.ም. ደግሞ የኮንጎ ብሔራዊ ነፃነትና አንድነት አደጋ ላይ በወደቀበት ጊዜ፥ በአስቸኳይ ወታደሮቿን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ስር በመላክ የኮንጎን ኅልውናና አንድነት እንዲድን ያደረገችው ኢትዮጵያ ነበረች። ዛሬ የራሷ ኅልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ዞር ብሎ ያያት የለም።

በሰባዎቹ ዓ.ም. እንደዚሁ፥ ናይጀሪያ ከሁለት ተከፍላ፥ በእርስ -በዕርስ ጦርነት ገብታ በነበረችበትና ኅልውናዋም ዓደጋ ላይ በወደቀበት ወቅት ሁለቱን ተዋጊ ወገኖች ማለት ተገንጣይዋን ባያፍራንና የማዕከላዊውን መንግሥት መሪዎቹን በቅርብ በማገናኘትና በማስማማት ነገሩ በሰላም እንዲፈፀም ጥረት አድርጋለች። የናይጀሪያ ሕዝብ አንድነትና የግዛቷም ልዕልና እንዲከበርም ሆኗል። ዛሬ ናይጀሪያ፥ በአፍሪካ ውስጥ ጠንካራ ሀገሮች ናቸው ከሚባልላቸው አንዷ እንደሆነች ይነገርላታል።

ኢትዮጵያ ግን ዛሬ አንድነቷ ተሸርሽሮ ፥ ሕዝቧ በብሄረሰብ ተከፋፍሎ፥ ኅልውናዋም እከርሰ መቃብር አፋፍ ላይ ደርሶና በቀጭን ክር ተንጠልጥሎ ይገኛል። ይህንን እያዩ የትላንትናዎቹ ባለውለታዎቿ " ዡሮ ዳባ " ብለዋል። ዛሬ ሀገራችን የታሪክ እንቆቅልሽ ሰለባ ሆናለች። የአፍሪካ ሕዝቦች በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ወድቀው ሲማቅቁ፥ በነበሩበት ወቅትና ለነፃነታቸው በሚታገሉበት ስዓት፥ ኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክ፥ የቆሳቁስ፥ የገንዘብ፥ የሞራልና የመሳሪያ ርዳታዋን አድርጋላቸዋለች። የብዙዎችን ሀገሮች የነፃነት ተዋጊዎችም አሰልጥናለች። የደቡብ አፍሪካን፤የናሚቢያን፥ ያንጎላን፥ የሞዛምብኪውን፥ የዝምባብዌን፥ የኬንያውን ማኦ ማኦ ንቅናቄንና የሌሎቹንም የነፃነት ተዋጊዎች ማስልጠኗ እንደ ዓብነት የሚጠቀሱ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ የረዳቻቸው አያሌ የአፍሪካ ሀገሮች፥ ሌላው ቢቀር፥ ዛሬ፥ የግዛት አንድነታቸውን ጠብቀው ይኖራሉ። ለ "ተላላዋ" ሀገራችን ግን፥ ደንታ ቀርቶ፥የዲፕሎማቲክ ትጎትና እንኳን ለማሳየት የሚያስገድዳቸው የኅሊና ሽልታ አላገኙም። የኢትዮጵያ ስደተኞችንም በየቦታው ሲያባርሩና ሲያሰቃዩ እየታዘብን ነው።

በ60ዎችም ዓመታት፥ ዓለም በሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ሰፈር ተመድባ የአሜሪካና የቀድሞዋ ሶቬየት ኅብረት የፖለቲካ ዳማ መጫወቻ መድረክ በነበረችበት ወቅት፥ የሁለቱ ኃያላን የጥቅም ፍክክርና የርዕዮተ-ዓለም ፍጭት ሰለባ ላለመሆን በማሰብ፥ የኃይል ሚዛ ቸውንም ለመጠበቅ የሚያስችል ፥ ሦስተኛ ኃይል መኖር አለበት ብላ በማመን፥ የገለልተኞች ሀገራት ጉባዔ እንዲመሠረት ያደረገች አንዷ ሀገራችን ነበረች። ይህች ሀገር ዛሬ ለራሷ ኅልውና በሞትና በሽረት ደረጃ ትገኛለች። የዛሬ ገዥዎቿም፥ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት እንድትወድቅ አድርገዋታል። እንግዲህ ይህች ካለፉት ስድሳ ዓመታት

ጀምራ፥ ለዓለምአቀፍ ፖሊቲካና ዲፕሎማሲ አስመስጋኝ አስተዋፅዖ በማድረግ፥ የራሷንም ክብር ያስጠበቀች ሀገር፥ ዛሬ በዓለም አቀፍ መድረክ የመጨረሻውን ቦታ ይዛለች:: በዚህም ታሪካዊ ጠላቶቿና ወያኔ የደስታ ዳንኪራ እየደነከሩ ይገኛሉ::

ከላይ በአጭሩ በቀረቡት ታሪካዊ ሀቆች ላይ ለማተኮር የተፈለገው፥ ኢትዮጵያ ለአለፉት ስድሳ ዓመታት የተከተለቻቸው የውጭ መመሪያዎች ሁሉ ትክክል ነበሩ አልነበሩም ? ጎድተዋታል-ጠቅመዋታል? ወደሚለው የክርክርና የትንታኔ አቅጣጫ ለማምራት አይደለም::ያ ወደፊት ከታሪካዊው ዕይታ ጋር እየተገናዘበ የሚታይ ይሆናል :: ያንን ማድረጉ አሁን በጣም አንገብጋቢና አጣዳፊ ፥ ብሎም ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ማለት ግን አይቻልም:: ዛሬ የእኛ ትኩረት ሊሆን የሚገባው፥ በአሁኑ የትግላችን ሂደት ውስጥ፥ ምን ዘዴና ብልኃት መጠቀም ይኖርብናል? ለትግላችን የሚጠቅም ርዳታ ከማንና? እንዴትስ ማግኘት እንችላለን? ይኖርብናል? እረ ለመሆኑ፥ ለትግላችን ርዳታ ያስፈልገናል? አያስፈልገንም? ለሚሉት ጥያቄዎች፥ መልስ ለመፈለግ የሚያስችለንን ታሪካዊ ምርኩዝም ሆነ ማጠየቂያ እማግኘቱ ላይ ነው:: እንዲያው ለነገሩ መደጋገሙ እንዳይሰለች እንጅ፥ ዛሬ ሀገራችን በዘር ተከፋፍላለች:: እንደ ሀገር የምትቆይበት ዕድሏም ከቀን ወደቀን እየጠበባት በመሄድ ላይ ነው:: ይህንም የሚያስፈፅም ችሎታ ያለው የአንድ ብሄረሰብ ቡድን በአገዛዝ ሥልጣን ላይ አለ:: በጨበጠው ሥልጣንና ማንተም እየተጠቀመ በፊርማው ሀገር አስገንጥሏል:: የሀገር ማስገንጠሉ ሂደት "ሕጋዊነት" እንዲኖረው ለማድረግ ራሱ በፃፈው "ሕገመንግሥት" ውስጥ የመገንጠል አንቀጽ አስፍሯል:: የወያኔ ሕገመንግሥት አንቀጽ 39፥ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወቅቱን እየጠበቀ የሚፈነዳ የተቀበረ ቦምብ ሆኗል:: ይህንን የተቀበረ ቦምብ ለማስወገድ የሚችል በአሁኑ ወቅት ሌላ ኃይል አለ? ወይስ ሁሉም በየፊናው ሙሾ መደርደር ብቻ ነው? ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ያሰፈሰፉት ኃይሎች አንቀጽ 39 ላለመጠቀም ምን የሚያግዳቸው ኃይልስ አለ? ሀገራችንን ለማዳን ሰማይ ወጥተን፥ ውቅያኖስ ገብተን፥ ካድማስ ባሻገር ሄደን ዕርዳታ የማንጠይቀበት ምን ምክንያት ይኖራል? ሀገራችንን ጅብ ከምናስበላ ጅብ በልተን የማንቀደስበት ምን የሚከለክለን የሞራልም ሆነ የታሪክ፥ የዕምነትም ሆነ የህግ ፍራቻ ይኖረናል? የነፃነት ትግል ያካሄዱ የዓለም ሕዝቦች ምንና እንዴት ያለ ርዳታ ያገኙ ነበር? መልሱ የሚገኘው ከራሱ ከባለቤቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሊሆን ይገባል::

በእኛ ዕምነት፥ በአሁኑ ተጨባጭ የዓለም ሁኔታ፥ ማንም ሀገር የኢትዮጵያን ችግርና አደገኛ ጥፋት በቅጡ የተገነዘበላት አለ ብለን አናምንም:: ልናድናትም ሆነ ልናጠፋት የምንችለው እኛው ራሳችን እንደምንሆን ግን እናምናለን:: በመሆኑም ራሳችን ተባብረን በመቆም፥ ከመታገል የተሻለ ሌላ አማራጭ አይኖረንም :: ይህ መሠረታዊ ዕምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፥ የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው የሚባለውን የሀገራችንን ይትበኃል ከቶም እንደ አማራጭ ማየት የለብንም ማለት ደግሞ የሚቻል አይመስለንም:: ሀገራችን ያጎረሰችባቸው እጀቿ አመድ አፋሽ ሆነዋል:: ተነክሰዋል:: ደምተዋል:: ጠላቶቿም አፌዘውባታል:: ተጫውተውባታል:: በሀገር በቀል ጠላቶቿ ደምታለች:: ሀገራችን ከራሷ አቅምና ችሎታ ተነስታ፥ በራሷ ተማምና፥ለራሷ

እስካልቆመች ድረስ፥ ማንም ዘወር ብሎ እንደማያያት ለሀገሩ ትንሳዔ ቆሚያለው የሚል ዜጋ ሁሉ ምን ጊዜም ከጭንቅላቱ ሊፍቀው አይቻለውም:: ስልትን ያቀፈና የሀገርን ጥቅም ያስቀደመ ብልኅ ፖለቲካና ግንኙነት ሊኖረን ይገባል:: ባዕዳን ሀገራችንን ነፃ ሊያወጡልን መጠበቅ የለብንም::በአንፃሩ ደግሞ የሀገር ወዳጆችን ለማብዛትና ወያኔን ነጥሎ ለማጥቃት ብቃቱ ሊኖረን ይገባል:: ወጣም ወረደም ግን ፀረ ወያኔ ትገላችን መፋፋሙና መቅደሙ ወሳኝ ጉዳይ ነው::

ትግላችን ይጠንክር!!!